Reading Is Fundamental.
until every child reads

# የውይይት መምሪያ ለቤተሰቦች




**ሰምቲንግ ሃፐንድ ቱ አወር ፕላኔት፤ ኪድስ ታክል ዘ ክላይሜት ክራሲስ (Something Happened to Our Planet: Kids Tackle the Climate Crisis)**

*ደራሲ፤  ማሪያኔ ሴላኖ እና ማሪየታ ኮሊንስ (*Marianne Celano and Marietta Collins)

*ሰዓሊ (Illustrator)፤* Bhagya Madanasinghe

**ይዘቶች (Themes)፤** አካባቢ እና ዘላቂነት (Environment and Sustainability)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ይህ መጽሐፍ ልጆች በራሳቸው ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች ላይ ለውጥ እንዲያደርጉ ያነሳሳቸዋል። የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖ፣ ለልጆች ተስማሚ የሆኑ ትርጓሜዎች፣ የናሙና ንግግሮች እና የአየር ንብረት ለውጥ ከልጆች ጋር ለመወያየት መመሪያን የያዘ የአንባቢ ማስታወሻን ያካትታል። ይህ መጽሐፍ በሃላፊነት በተሰራ ወረቀት ላይ በአትክልት ላይ በተመሰረቱ ቀለሞች ታትሟል።

## ጮክ ብለው ያንብቡ

**ከንባብ በፊት፤ መሰረት ይገንቡ (Build Background)**

- ርዕሱን ለማስተዋወቅ ስለ አየር ንብረት ለውጥ አጭር ቪዲዮ ይመልከቱ።

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ (Make Connections)**

- ገፀ ባህሪያቱ ከጉንዳን ጋር እንዴት ይመሳሰላሉ? ከታሪኩ ምሳሌዎችን ተጠቀም።
- ገፀ ባህሪያቱ ፕላኔቷን ለመርዳት የተባበሩበት አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?
- መምህራቸው ምን ዓይነት ሀሳብ ሰጣቸው እና እንዴት ይጠቅማል? ተገናኝ፤ አንድ አስተማሪ ጠቃሚ ሀሳብ ሰጥቶህ ያውቃል?
- ከርዕሰ መምህሩ ጋር ያለው ስብሰባ ወደ አዲስ እቅድ እንዴት ይመራል? እቅዱ የተሳካ ነበር? ዝርዝሮችን ከመጽሐፉ ተጠቀም።

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- ችግሩን ለመፍታት ገጸ ባህሪያቱ እንዴት አብረው ሠሩ? የአየር ንብረት ለውጥን ለመርዳት በጋራ የምንሰራባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህን መጽሃፍ ከወደደ፤ የሚከተሉትን ከግምት ያስገቡ፤**

- በሌሎች ንግግሮች ጊዜ ስለ እሱ እንዲያወሩ አበረታቷቸው።
- በተዛማጅ መጽሃፍት እና ሪሶርሶች (resources) ስለ ዘላቂነት (sustainability) የበለጠ ለማወቅ የአር አይ ኤፍን (RIF’s) Sustainable Futures ማዕከልን ይመልከቱ።


©2024 Reading Is Fundamental